.

## *አስተያየት*

## *ልጓም በሌለው ፈረስ ላይ መገለብ ውድቀትን ያስከትላል*

*ይህን አስተየየት እንድጽፍ ምክንያት የሆነው ቅዳሜ ነሐሴ 11 ቀን 2005 ዓ.ም ( Saturday, August 17, 2013 )አቶ አበበ በለው ብቻቸውውን በባለቤትነት በሚመሩት አዲስ ድምፅ ሬድዮ ጣቢያ ላይ ኢሕአፓን በሚመለከት ያስተላለፉት ዜናና ቃለ መጠይቅ ነው ። አንድ ጋዜጠኛ ለሕዝብ የሚያቀርበው ዜና ሚዛናዊና እውነት ላይ የተመረኮዘ መሆን እንዳለበት የሙያው ዘርፍ ጥናት ያረጋግጣል። እርሳቸው ግን ከላይ በተጠቀሰው ቀን ‘‘ኢሕአፓ ነን’’ በኢሕአፓ ውስጥ” እርማት እንቅስቃሴ’’ እንዲካሄድ እንፈልጋለን እያሉ ሁለት የድርጅቱን አመራር አባላት አብራርናል ለሚሉና ከድርጅቱ ለተበራሩ ሁለት ግለሰቦች መድረክና ሰፊ ጊዜ በመስጠት በኢሕአፓ ላይ የውሸት ፕሮፓጋንዳ እንዲያካሄዱና ሕዝብን ውዥንብር ውስጥ እንዲከቱ ተደርጓል። ለዚህ እንደአንድ አድማጭ መረጃ የሆነኝ አንድ አድማጭ እነዚህን ግለሰቦች በኢሕአፓ ጉዳይ ለመነጋገር ሁኔታዎችን ሲያመቻቹ እርስዎ ባሉበት ከተማ በዋሽንግተን ዲሲ የሚገኛውን የድርጅቱን ጽ/ቤት ደውለው ቃለ መጠይቅ እንዲሰጡ ስለጋበዙት ግለሰቦች ምንነት ለምን ለማወቅ ጥረት አላደረጉም ተብሎ ለተጠየቀው ጥያቄ የሰጡት መልስ አርስዎና ያቀረቡት ግለሰቦችዎ የቆማችሁት መሰረት ውሸት ነው እንዲል አስገድዶኛል። ለጥያቄውም የሰጡት መልስ፡- ኢሕአፓ ጽ/ቤት ሁልጊዜ ሲሄድ የሚያገኘው ዘርጋውንና አቶ እገሌን ነው (እገሌ ያልኩት ኢሕአፓዎች በማይፈለግ ቦታ የሰውን ስም የማይጠሩ ስለሆነ ትምህርት ይሆንዎ ብየው ነው። አንድን ትልቅ ሰው ከማይመስል ሁኔታ ጋር ለማገነኘት አይሞክሩ። ) ፣ አቶ ዘርጋው የኢሕአፓ አመራር መሆኑን አውቃለሁ ፣ወደ ጽ/ቤቱ ስልክም ሲደውል የማገኘው አቶ ዘርጋውን ነው ፣ ከድርጅቱ መበራረቻው ለእኔ አልደረሰኝም በማለት መልስ ሰጥተዋል። እንዴትና በምን ዓይነት የጋዜጠኝነት ሙያ ነው በኢሕአፓ ጽ/ቤት ያገኙት ግለሰብ/ ግለሰቦች ሁሉ የኢሕአፓ አመራር ነው የሚሉት? በኢሕአፓ ጽ/ቤት ተገኝቶ ስልክ የሚያነሰ/የሚያነሱ ግለሰቦች ሁሉ የኢሕአፓ አመራር ነው ብለው ምስክርነት እንዲሰጡ ሙያዎ ይፈቅዳል? አቶ ዘርጋው የኢሕአፓ አመራር መሆኑን አውቃለሁ ብለው አፍዎን ሞልተው ምስክርነት ሰጥተዋልና መቼና በየትኛው ጉባኤ እንደተመረጠ መነገር ይችላሉ? የኢሕአፓ አባል ኖት? አባል እንዳልሆኑ በቃለ መጠይቁ ወቅት ስያስተላልፉ በነበሩት መልእክት ስለሚረዳ ለዚህ መልስ ከእርስዎ አልሻም። ለእርስዎ እንዴት ነው ኢሕአፓ ከድርጅቱ ያባራረቻውን ግለሰቦች የሚያሳውቅዎ? ከየትኛውስ የድርጅት አሠራር ነው ወይም የጋዜጠኝነት ሙያ ነው እንደዚህ ዓይነት አካሄድ የተማሩት?ሁለቱም ግለሰቦች በተለይም አቶ ዘርጋው ከደርጅቱ የተባራሩ መሆኑን በራሱ አፍ ተነግሯል። ከድርጅቱ የተወገዱ ግለሰቦችን ድርጅት ውስጥ እንዳሉ አድርጎ ማቅረብ ፣ ሕዝብ ውስጥ ውዥንብር መንዘት የአርስዎ ፍላጎት እንደሆነ ካቀረቡት ጥያቄዎችና ሰያሳዩ ከነበረው ሚዛናዊነት ከጎደለው አስተያየቶችዎ ለማወቅ ችየለሁ።*

*በሌላ ጥያቄዎ ደግሞ እንዲህ ብለው ነበር። “እኔ በጣም ነው የሚከታተለው የኢሕአፓን ጉዳይ “ ፤”አሁን ወሳኝ (decessive majority) የብዙሃን ድምፅ አላችሁ? የብዙሃን ድምፅ የሚናያበት ወቅት አሁን ነው ትላላችሁ?“፤ እስካሁን መኻል መግበት ያልቻልነው የትኛው የብዙሃን ድምፅ እንዳለው ስላላወቅን ነው “ በማለት ጠይቀዋል። እርስዎ የኢሕአፓን ጉዳይ ለመከታተል ማን ኖት? የተለየ የቤት ሥራ ተሰጥቶዎት ይሁን? እንዴትስ በድርጅቱ የውስጥ ጉዳይ ለመግበት ምኞት አደረብዎ? ድርጅቱ እውነት ለሁለት ተከፍሎ የብዙሃን ድምፅ አግኝቷል ብለው የጠላት ምክር እንዴትስ ለመስጠት ፈለጉ? ግን ለምን ይሁን ወዳጅ መስሎ በዚህ እውነተኛ ኢትዮጵያዊ ድርጅት ላይ ይህ ሁሉ ዘመቻ የሚካሄደዉ?*

*ከውስጥም ሆነ ከውጭ የኢትዮጵያ ጠላቶች በኢሕአፓና ሌሎች ኢትዮጵያዊ በሆኑ ድርጅቶች ላይ የተቀነባበረ ዘመቻ ከፍተዋል። በቢሊዮን የሚገመት ገንዘብም እየረጩ ነው። ከሰሞኑም በዋሽንግተን ዲሲና በአውሮፓ ከፍተኛ ገንዘብ ወያኔ እየረጫ ነው።ከዚያ ከሚረጫው ገንዘብ የሚያገኙ ፣ የኢትዮጵያ ጠላቶች የሆኑት ወያኔና ሻዕቢያ ፣በአዲስ አበባና በተለያዩ ቦታዎች ቤት የሰሩ ፣ መሬት የተመሩ ፣ የተለያዩ እንቬስትመንት በአገሪቱ ውስጥ ያደረጉና ለማድረግ የሚፈልጉ በሕዝብ ላይ የሚፈጸመውን በደል እያዩ እናዳላዩ ሆነው አዲስ አበባ ፎቅ በፎቅ ሆነለች የሚሉ የግል ኑሮና ግለኝነት ያጠቃቸው ግለሰቦች ፣ በውጭ ሆነው ሬድዮ ጣቢያ ከፍተው ሕዝብን መስለው የወያኔ ተቃዋሚ ነን እያሉ በተለያዩ ቦታወች ቤት ለሰሩት ወያኔ የቤት ባለቤትነትን የከለከላቸው ጋዜጠኞችና ሌሎች፣ እውነተኛ ተቃዋሚ ሳይሆኑ የኢትዮጵያን ስም የያዙ ወደ ወያኔ ጉያ ለመግበት የሚመኙ አስመሳዮችና ተገንጣዮች ፣ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን የሚጠሉ፣ ለውጭ ኃይሎች የተገዙ ከሀዲዎች ፣ ከራሱ ከኢሕአፓ የወጡ አንጃዎችና ከድርጅቱ የተወገዱት ፣ የአጼ ኃይለስላሴ ሥርዓት ናፋቂዎች ፣ በደርግ ሥርዓት እጃቸው በንጹሀን ወንድሞቻችን፣ እህቶቻችን ፣ አባቶቻችን ፣ እናቶቻችን--ወዘተ ደም የተጨመለቁ ሁሉ፤ የጥቃት በትራቸውን በአብዣኛው የሚያሳርፉት በኢሕአፓ ላይ ነው ።የአርስዎም ምድብ የትኛው ይሁን የሚል ጥያቄ እንዲያነሳ በውይይቱ ወቅት ስያነሱ ከነበሩት ጥያቄዎችና አስተያየትዎ አስገድዶኛል ? ይዋል ይደር እንጂ ይደርስበታል ለዚያ አይጨናቁ*

። የኢሕአፓዎችን ጉዳይ ለነሱ ትተው፣ ኢሕአፓንም ለቀቅ አድርገው ቀስትዎን በወያኔ ላይ ብወርውሩ የተሻለ ይሆናል። በመረጃ ላይ ያልተደገፈ ዜና ማቅረብም ልጓም በሌለው ፈረስ ላይ መገለብ ሆኖ ውድቀትን ያስከትላል። ሕዝብን ያሳስታል ። ወገኔ ከዚህ ዓይነት ድርጊት ይቆጠቡ ። ኢትዮጵያ ብዙ ጀግኖችን አጥታለች ። አገር አጥፊዎችንና ሰላዮችን ስናስነግስና በስልጣን እንዲቀመጡ በማድረግ አገሪቱን ለዚህ ያደረስንበት ቆሻሻ ታሪክ አለን። ከዚህ እንውጣ። ዛሬም በሁለቱ የኢሕአፓ አመራር አባላት ላይ የሚካሄደው ዘመቻ የዚያ ቅጥያና አካል ነው። የውጭዎቹ ጥቃት መሪ አሳጥተው ጥቅማቸውን ለማስከበር ነው። የእኛዎቹ የእነሱ መሳሪያ መሆን ግን በአገር ላይ የሚካሄድ ክህደት ነው ። አስፋሪ ተግባር ነው። አገርና ሕዝብ ግን ከሁሉም በላይ ነው። አገርንና ሕዝብን እናስቀድም ። ዘረኝነትንና መንደርተኝነትን እናስወግድ ። ኢትዮጵያን የጀግኖች አልባ ለማድረግ የሚደረገውን የተቀነባበረ ሴራ ማክሸፍም የሁሉም ኢትዮጵያዊ ግዴታ መሆን ይገባል። ጋዜጣኞች ለዚህ እውነት መቆም ይጠበቅባቸዋል።

ሌላው የሚያስቀው ቀልድ ጠቅላላ ጉባኤ ገና ይካሄዳል ስሉ የተደመጡት እንግዶችዎ ሁለቱን በጠቅላላ ጉባኤ የተመረጡ የድርጅቱን አመራር አባላት በየትኛው ስልጣን ነው ያባራሩት? ይህች ናት የልጅ ጨዎታና የዝቅጠት ምልክት። ኢሕአፓ ትልቅ ድርጅት ነው ። ከድርጅቱ በተባራሩ በተወሰኑ ግለሰቦች የሚላካ አይመስለኝም ። ከኢሕአፓ በሆነውም ሆነ ባልሆነው ምክንያት የወጡ ግለሰቦች ወደ ድርጅቱ እንዲመለሱ ጥሪ እንግዶችዎ ሲያደርጉ አደምጨለሁ። በሆነው ምክንያት የወጣው አባል ለምን ይመለሳል ብለው ጥያቄ አልጠየቁም? እንዲያውም ስደግፉ ነው የነበሩት ። ከድርጅቱ አንጃ በመሆን ስንት ሕይወት ያጠፉ ወንጀለኞች ፣ ሰላዮች ፣ ጋራፊዎች ፣ የድርጅቱን ንብረት ዘርፈውና ቀብረው የወጡ ወንጀለኞች አሉ እንዴት እነዚህ እንዲመለሱ ጥሪ ይተላለፋል? የዛሬ አፈጮሌዎች የእርስዎን አንዱን እንግዳ ጨምሮ የድርጅቱን መሳሪያ ቀብረው የጠፉ አሉ ። አስኪ ስለዚህ ጉዳይ በበለሰ ውስጥ በሠራዊቱ ውስጥ የእርማት እንቅስቃሴ ተደርጓል ያለውን ግለሰብ ከነበረከት ስምዖን ጋር የነበረውን ግንኙነትና የፈጸመውን ድርጊት ጠይቀው ይረዱ ። ደርግና ተባባሪዎቹ በአገሪቱ በሙሉ የኢሕአፓ አባላትን በሚገድሉበት ፣ አስከሬናቸው በየመንገዱ በሚጣልበት ፣ ለቤተሰብ አስካሬን ከምንልክ ሆስፒታልና ከሌሎችም ቦታዎች ለመውሰድ የተገደሉበት የጥይት ዋጋ ክፈሉ በተበለበት ፣ ወንድምና እህት ገድለው አባትንና እናትን በግድያው ደስ ብሎናል ብላችሁ ጨፍሩ ተብለው በተጠየቁበት ፣ አስረው የተለያዩ ስቃይ በሚያደርሱበት ወቅት በኢሕአፓ ሠራዊት (በኢሕአሠ) ውስጥ እርማት እንቅስቃሴ እናደርግ ባዮቹ ቀንደኛ አቀንቃኞች ሠራዊቱን ለመበተን የአመራር አባላትን ለማጥፋት ብዙ ጸረ-ድርጅት ተግባር ፈጽመው የእና በረከት ስምዖን ቡድን ወደ ወያኔ ገብቶ ኢሀዲን( የኢትዮጵያ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ) ተብሎ ኋላም ወደ ዘረኝነት ተለውጦ ብአዴን ( ብሔረ አማረ ዴምክራሲያዊ ንቅናቄ) ሆኖ ዛሬ አገራችንን እያጠፉ ይገኛል። የቀሩት ደግሞ የድርጅቱን መሳሪያ ቀብረው ወደ ውጭ በመውጣት ደርጅቱ ውስጥ ድምፃቸውን አጥፍተው እንደቆዩ አንዱ እንግደዎ ኢሕአፓ ውስጥ እርምት እምቅስቃሴ የተጀመረው ከሶስተኛ ጉባኤ ጀምሮ ነው በማለት ተነግሯል። እንዚህ አስመሳዮች አቅርበውት የነበረው ጥያቄ ኢሕአፓ አገር ቤት ገብቶ ለመሥራት እንድችል ለወያኔ የይቅርታ ደብዳቤ ይጻፍ ፣ ወያኔን ወያኔ/ኢሀአዲግ ከማለት ኢሀአዴግ እንባል የሚሉና ሌሎችም ነበሩ ። ይህ ድርጅቱን ሸንፋት ላይ ለመጣልና ለማስጠቃት የሞከሩት ሀሳብ በአባላት ወድቅ ሲሆንባቸው በድርጅቱ ውስጥ አንጃ ለመፍጠር ሲንቀንቃሱ ተደረሳበቸው ። የሀሳብ ልዩነታቸውን እንዲያቀርቡና ውይይት እንዲካሄድ ድርጅቱ ልዩ ጉባኤ ሲያዘጋጅ ፈስ ያለበት ዝላይ አይችልም ሆኖ የነገሩ ቀንደኛ መሪያቸው ማታ ጠፍቶ የቀሩት ለጉባኤው ቀርበው ሀሳባቸውን ሳይገልጹ ፈርጥጠው ኢሕአፓ ( ዲሞክራሲያዊ) ሆነን ብለው ለመጀመሪያ ጊዜ በድርጅቱ ታሪክ ተለጣፊ ለመመስራት ብንፈርገጡም የትም ሳይደርሱ ቀርተው ወያኔም በድርጅቱ እንዲደርስ ፈልጎት የነበረው አደጋ በአለመድረሱ ተነዶ ወግዱ አላቸው ። የሚገቡበት ሲጠፈ ሕብረት ሕብረት ማለት ጀመሩ ። ሌላው የእነዚሁ ተቀጥላ የሆኑት እንግዶችዎ ለነሱም ሆነ ለሌሎች በድርጅቱ ላይ ወንጀል ለፈጸሙት ጥሪ እያዳረጋላቸው ነው። እነዚህ ድርጅት ውስጥ ምስጥ ሆነው የቆዩት ዛሬ ከእና በረከትም ጋር ግንኙነት በመፍጠር በሚደረግላቸው የገንዘብ እርዳታና አንዳንድ ድርጅቶችን ለመከፋፈል በሻዕቢያና በወያኔ የተቋቋሙ ድረ-ገጾችንና ሬድዩ ጣቢያዎችን በመጠቃም በድርጅቱ ላይ “የእርማት እንቅስቃሴ እንዲደረግ እንፈልጋለን ” በሚል ሽፋን እየዘመቱ ናቸው ። ይህንንም በደንብ ይገንዘቡ ወገኔ። የኢሕአፓ ወክንድን ወክሎ እንዲነገር መድረክ የሰጡትም ግለሰብ ከድርጅቱ በድስፕሊን ጉድለት የተወገደ ለመሆኑ የወጣት ክንፉ ዓለምአቀፍ አመራር የሰጠው መግለጫ በተለያዩ ድረ-ገጾችና ሬድዮ ጣቢያዎች ለሕዝብ ይፋ ሆኖ እያለ ስለጉዳዩ መግለጫ ያወጡትን ዓለምአቀፍ አመራር ሳይጠይቁ በድርጅቱ ወጣት ክንፍ እንቅስቃሴም ላይ ጣልቃ ገብተዋል ። በአንግዶችዎ ላይ የተቃውሞ አስተያየት ያቀረቡ አድማጭዎችዎን ሀሳብ እንዳይሰጡ ጊዜ የለኝም በሚል ሰበብና አስተያየት አቅራቢዎችን በሚመለከት የተሰጠውንም ጥቆማ በመጠቃም ኢትዮጵያዊ ጫዋነት በጎደለው ሁኔታ አቶ ዘርጋው የተባለው እንግደህ የሎሌና የጌታ ተረት እየተነገረ ስሳደብ ዝም ብለው ለቀቁ ። እዚያ ትውልድ ትልቁ እንቅስቃሴ የሎሌና የጌታን ሥርዓት ለማስወገድ ነበረ። ዛሬ ኢሕአፓ ነበርኩ ከሚለው ግለሰብ ያንን ተረት እንደገና ለማስማት አልነበረም ። ያ የፈውዳል ሥርዓት ነፃብረቅ ነው። እንደዚህ ዓይነት ጉዳዮችን ዝም ማለት በስራዎ ላይ ሰዎች እምነት እንዲያጡ የሚያደርግና ሚዛናዊነት የጎደለው ተግባር ነው ። ማረም ይገባዎታል። ዜና ወይም መረጃ እውቀት ነው የውሸት ዜና ( Disinformation) ከፍተኛ ጉዳት በአገርና በሕዝብ ላይ ያደርሳል። ወገኔ ጥንቃቄ ያደርጉበት። መገነኛ ብዙሃን የእውነት ማስተላለፊያ ቱቦ መሆን ይገባቸዋል። በዘርፉ የተሳማሩትም ኃላፊነታቸውን በአግባቡ መወጣት ይኖርባቸዋል ። ይህ ሲደረግ ብቻ ነው ሕዝቡ በማካሄድ ላይ ለአለው ትግል አስተዋጽዖ

*የሚያደርጉት ። ኢትዮጵያዊ ድርጅቶችን እንደ ኢሕአፓ ያሉትን እንዲደከሙ ከማድረግ ተቆጥቦ እንዲጣናከሩ መርዳት ያሰፈልጋል።*

*በኢሕአፓ ላይ የተከፈተው የተቀነባበረ ዘመቻ መቆም አለበት። ከሕዝብ ያጣላል ።ይህን ድርጅት የኢትዮጵያ ህዝብ የሚወደው ድርጅት መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል ። በዚህ ድርጅት ላይ ጥቃት ለማካሄድ መሞከሩ ትርፉ ኪሳራ ነው ፤ ትግሉን መጉደት ነው። ለወያኔ ዘንግ ማቀበል ነው። የጊዜ ጉዳይ ቢሆን እንጂ ኢሕአፓና ሌሎች ኢትዮጵያዊ ድርጅቶች ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር በመሆን ጠላቶቹን ያሸንፋሉ።*

*ሳሙኤል በረከት*
*ከሰሜን አሜሪካ*